DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF EDUCATION

በልግ 2015

የተከበሩ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

በዲሲ ግዛት የትምህርት ጉዳይ ዋና ተቆጠጣሪ/ሱፐርኢንቴንደንት ቢሮ በግዛቱ ውስጥ በሚገኙት ሁሉም ትምህርት ቤቶች በ2015-2016 ዓ.ም የክረምት የዝግ ወቅት ከመንግስት እና የመንግስት ቻርተርድ ትምህርት ቤቶች ጋር በትምረት በመሆን በኮሎምቢያ ግዛት ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ለአደጋ ያላቸዉን የተጋላጭነት ባህሪ ለማጥናት የሚያስችል ዳሰሳዊ ጥናት ያካሂዳል:: **ልጅዎት በዚህ ዳሰሳዊ ጥናት ላይ ተሳትፎ እንዳያደርግ የሚፈልጉ ከሆነ የዚህን ደብዳቤ የመጨሻ ክፍል በመሞላት ወደ ትምህርት ቤቱ ይመልሱት::**

የወጣቶች የአደጋ ተጋላጭነት ባህሪ ዳሰሳዊ ጥናቱ በዩናይትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካ የሚገኙ ታዳጊዎች እና አዋቂዎች ለሞት አደጋ፣ ለአካል ጉዳት እንዲሁም ለማህበራዊ ቀዉሶች የሚያጋልጡዋቸዉን ባህሪያት ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል ዳሰሳዊ ጥናት ነዉ:: ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጣቸዉ ለጤና አደጋ የሚያጋልጡ ባህሪያት ያልታሰበባቸዉ አደጋዎች እንዲሁም ጥቃቶች፣ ወሲባዊ ባህሪያት፣ አልኮሆል እና ሌሎች አደንዘዥ እጾችን መጠቀም፣ ሲጋራ ማጨስ፣አግባብ ያልሆነ አመጋገብ፣ እንዲሁም በቂ ያልሆነ አካላዊ እንቅስቃሴ ናቸዉ:: የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ በዋነኝነት በሁለት የጤና ጠንቆች ዙሪያ መረጃን ያሰባስባል፣ እነሱም ከልክ ያለፈ ዉፍረት(ኦቤሲቲ) እና አስማ ናቸዉ:: ሪፖርት የሚደረጉትን ዳታዎች በማሰባበስ በአሜሪካ የሚገኙ ወጣቶች ያላቸዉን ወሲባዊ ባህሪያት ለአካባቢዉ ማህበረሰብ፣ ለሀገራዊ ትኩረት፣ እንዲሁም አልፎ አልፎ ለአለም አቀፍ የትኩረት አቅጣጫነት ጥቅም ላይ የሚያዉለዉ ሲሆን በመታየት ላይ ያሉ አዝማሚያዎችን ለመመርመር እንዲሁም በጊዜ ሂደት የታዩ ለዉጦችን ለመገምገም ጥቅም ላይ ይዉላል:: ተጨማሪ መረጃዎችን ቀጥሎ ከተመለከተዉ ድረ-ገጽ ማግኘት ይችላሉ:
http://www.cdc.gov/HealthyYouth/yrbs/index.htm

ይህ ዳሰሳዊ ጥናት በመጠይቅ ፎርማት የተዘጋጀ ሲሆን በአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች በአንድ ክፍለ ጊዜ ማለትም በ45 ደቂቃ ውስጥ የሚሞሉት መጠይቅ ነዉ:: በመጠይቁ ላይ የተማሪዎች ማንነት ተለይቶ የማይገለጽ ስለሆነ ተማሪዎች ነጻ ሆነዉ ለሁሉም ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ እንዲሰጡ ኣጋጣሚዉን ይፈጥርላቸዋል:: ይህ ዳሰሳዊ ጥናት በተማሪዎች መልካም ፈቃድ የሚከናወን እንደመሆኑ ተማሪዎች መጠይቁን ባለመሙላታቸዉ ምክኒያት የሚደርስባቸዉ ቅጣት አይኖርም፣ ሆኖም ጥናቱ አስፈላጊ በመሆኑ ምክኒያት የተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እጅግ ይበረታታል::

ልጅዎት በዚህ ዳሰሳዊ ጥናት ላይ የሚሳተፍ ከሆነ ሌላ ተጨማሪ ድርጊት አይጠበቅበትም:: ሆኖም ልጅዎት በዚህ ዳሰሳዊ ጥናት ላይ እንዲሳተፍ የማይፈልጉ ከሆኑ ከታች የተመለከተዉን ክፍል በሙላት፣ ከፈረሙ በኋላ ልጅዎት ወደ ሚማርበት ትምህርት ቤት በመሄድ ከአክቶበት 1፣2015 ዓ.ም በፊት ባለዉ ጊዜ ውስጥ ያስገቡ:: ጥያቄ ካልዎች እባክዎን የልጅዎትን መምህራን ወይም ርእሰ መምህራንን በማነጋገር ምላሽ ያግኙ:: በተጨማሪም ሚ/ር ካፉኢ ዶኢ በዚህ ስልክ ያነጋግሩ 202-741-6484 ወይም በዚህ የኢሜይል አድራሻ ይተቀሙ osse.hydt@dc.gov.

ከሰላምታ ጋር፣

Unique Morris-Hughes, Ph.D.
Chief Operating Officer
Office of the Chief Operating Officer (COO)

የተማሪው ስም: _____

ትምህርት ቤት: _____ ክፍል: _____

ይህንን ቅጽ አንብቤ ስለ ምን ጉዳይ እንደሆነ ተገንዝቤያለሁ::

[ ] አያይ፣ ልጄ በዚህ ዳሰሳዊ ጥናት ላይ ባይሳተፍ እመርጣለሁ::

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ: _____ቀን: _____

የወጣቶች የአደጋ ተጋላጭነት ባህሪ ዳሰሳዊ ጥናት መረጃ

ጥ. ይህ ዳሰሳዊ ጥናት ለምን አላማ በመደረግ ላይ ይገኛል?

መ. የወጣቶች የአደጋ ተጋላጭነት ባህሪ ዳሰሳዊ ጥናቱ በዩናይትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካ የሚገኙ ታዳጊዎች እና አዋቂዎች ለሞት አደጋ፣ ለአካል ጉዳት እንዲሁም ለማህበራዊ ቀዉሶች የሚያጋልጡዋቸዉን ባህሪያት ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል ዳሰሳዊ ጥናት ነዉ:: ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጣቸዉ ለጤና አደጋ የሚያጋልጡ ባህሪያት ያልታሰበባቸዉ አደጋዎች እንዲሁም ጥቃቶች፣ ወሲባዊ ባህሪያት፣ አልኮሆል እና ሌሎች አደንዘዥ እጾችን መጠቀም፣ ሲጋራ ማጨስ፣አግባብ ያልሆነ አመጋገብ፣ እንዲሁም በቂ ያልሆነ አካላዊ እንቅስቃሴ ናቸዉ:: የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ በዋነኝነት በሁለት የጤና ጠንቆች ዙሪያ መረጃን ያሰባስባል፣ እነሱም ከልክ ያለፈ ዉፍረት(አቤሲቲ) እና አስማ ናቸዉ:: ሪፖርት የሚደረጉትን ዳታዎች በማሰባበስ በአሜሪካ የሚገኙ ወጣቶች ያላቸዉን ወሲባዊ ባህሪያት ለአካባቢዉ ማህበረሰብ፣ ለህገራዊ ትኩረት፣ እንዲሁም አልፎ አልፎ ለአለም አቀፍ የትኩረት አቅጣጫነት ጥቅም ላይ የሚያዉለዉ ሲሆን በመታየት ላይ ያሉ አዝማሚያዎችን ለመመርመር እንዲሁም በጊዜ ሂደት የታዩ ለዉጦችን ለመገምገም ጥቅም ላይ ይዉላል:: ተጨማሪ መረጃዎችን ቀጥሎ ከተመለከተዉ ድረ-ገጽ ማግኘት ይችላሉ:.

ጥ. በዚህ ጥናት ውስጥ በግላዊ የጤና ጉዳዮች ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎች አሉ?

መ. አዎ:: በእርግጥ አንዳንድ ጥያቄዎች ግላዊ ቢሆኑም መልሶቹ እና የመላሾች ማንነት በሚስጥር ተጠብቀዉ ይቆያሉ:: አላግባብ የሆነ ዉፍረት፣ አመጋገብ፣ የአእምሮ ጤና፣ ኤችአይቪ/ኤድስ ኢንፌክሽን፣ እንዲሁም በግብረስጋ ግኙኝነት የሚተላለፉ በሽታዎች/ኤስቲአይ/ ዋና ዋናዎቹ የጤና ጠንቆች ናቸዉ:: ለኤችአይቪ/ኤድስ ኢንፌክሽን፣ እንዲሁም በግብረስጋ ግኙኝነት የሚተላለፉ በሽታዎች/ኤስቲአይ/ዋና ዋናዎቹ የመተላለፊያ መንገዶች ግብረስጋ ግኙኝነት እና በደምስር በኩል የሚወሰዱ አደንዛዥ እጾች መሆናቸዉ ይታወቃል:: ወጣቶች ለዚህ አደጋ ተጋላጭ መሆናቸዎን ለማረጋገጥ የሚቻለዉ እነዚህኑ ወጣቶች በመጠየቅ ነው::በዚህ ዳሰሳዊ ጥናት ውስጥ ከሚቀርቡት አንኳር ጥያቄዎች መሀከል የእራስን ህይወት ለማጥፋት የሚደረግ ሞከራ፣ ሲጋራ ማጨስ፣ አልኮሆል እና ሌሎች አደንዛዥ እጾችን መጠቀም፣ እንዲሁም የጦር መሳሪያ ይዞ መንቀሳቀስ ይገኙበታል:: ጥያቄዎቹ ቀጥተና በሆነ መንገድ በጽፍ ይቀርባሉ::

ጥ. የተማሪዎች ስሞች ይገላጻሉ ወይም ከጥናቱ ጋር ተያይዘዉ ይነሳሉ?

መ. አያይ:: በጥናቱ ላይ የግለሰቦች ማንነት እና የግል መረጃዎቻቸዉ በሚስጥር ተይዘዉ ይቆያሉ:: በዚሁ መሰረት የእርስዎ ልጅ ስም እና የግል መረጃዎቹ በሚስጥር ተጠብቆ እንዲቆይ ታቅዶ የተዘጋጀ መጠይቅ መሆኑን ልናረጋግጥልዎ እንወዳለን::

ጥ. ተማሪዎች በባህሪያቸዉ ላይ የታየዉን ለዉጥ ለመገምገም እንዲቻል ደጋግመዉ መሳተፍ ይችላሉ?

መ. አያይ:: የተማሪዎች ስም በጥናቱ ላይ የማይገለጽ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በግለሰቦች የጤና ሁኔታ ላይ የሚታየዉን ለዉጥ ለይቶ ማወቅ አይቻልም::

ጥ. የእኔ ልጅ በጥናቱ ላይ እንዲሳተፍ የተመረጠዉ በምን ዓይነት ሁኔታ ነዉ?

መ. የእርስዎ ልጅ የተመረጠዉ ባለበት የክፍል ደረጃ መሰረት ነዉ፤ እንዲሁም በኮሎምቢያ ግዛት ውስጥ ያሉ ሁሉም የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይህ ጥናታዊ ዳሰሳ ይደረጋል::

ጥ. ይህን ጥናታዊ ዳሰሳ ለመሙላት ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?

መ. ይህ ጥናታዊ ዳሰሳ በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ እንዲሞላ ታስቦ ነው የተዘጋጀዉ::(ይህም በግምት 45 ደቂቃ)

ጥ. የእኔ ተማሪ የሚጠየቃቸዉን ጥያቄዎች ለማየት እችላለሁ?

መ. አዎ፣ የዚህ መጠይቅ ኮፒ እስከ ሴፕቴምበር 15 ቀን፣ 2015 ጀምሮ በልጅዎት ትምህርት ቤት ይቀመጣል:: በተጨማሪም ከዚህ ቀደም የተደረጉ ዳሰሳዊ ጥናቶች በዚህ አድራሻ ሊያገኙ ይችላሉ: http://osse.dc.gov/service/youth-risk-behavior-survey

ጥ. ምናልባት ልጄ ወይም እኔዉ እራሴ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ተጨማሪ እዉቀት ወይም የድጋፍ ምንጭ ቢያስፈልገንስ?

መ. ይህን የወጣቶች የአደጋ ተጋላጭነት ዳሰሳዊ ጥናት ከሞሉ በኋላ ሁሉም ተማሪዎች እና አሳዳጊዎቻቸዉ የሚፈልጉትን መረጃ እና ድጋፍ ለማግኘት የሚያስችላቸዉ ስርአት ያለ ሲሆን በዚሁ መሰረት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፤ የከተማ አስተዳደሩ ቢሮዎች፣ እንዲሁም ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት እና አድራሻዎቻቸዉ የሚገልጽ ወረቀት ለልጅዎት እንዲሰጠዉ ይደረጋል:: የዚህ ወረቀት ኮፒ በልጅዎት ትምህርት ቤት የሚቀመጥ ሲሆን ባስፈለግዎት ጊዜ እርስዎም ሊያዩት ይችላሉ::

ጥ. ከዚህ ዳሰሳዊ ጥናት የሚገኘዉ መረጃ በምን ዓይነት ሁኔታ ጥቅም ላይ ይዉላል?

መ. ከዳሰሳዊ ጥናቱ ተሳታፊዎች የሚሰበሰበዉ መረጃ ሙያዊ ትንታኔ ከታከለበት በኋላ በሀገር አቀፍ ደረጃ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ለማዉጣት እንዲሁም ፈንድ ለማከፋፈል ጥቅም ይሰጣል:: ካለፉት ዳሰሳዊ ጥናቶች የተገኙት ዉጤቶች ከዚህ ድረ-ገጽ ማግኘት ይቻላል: www.osse.dc.gov. በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጠናቀረዉ መረጃ በበሽ መከላከል እና ቁጥጥር ማእከላት ጥቅም ላይ የሚዉል ሲሆን የ2015 ዳታ ሲለቀቅ ከዚህ ድረ-ገጽ ማግኘት ይቻላልሰ www.cdc.gov/HealthyYouth/index.htm.